አይርላድ

An Roinn Dlí agus Cirt,
Gnóthaí Baile agus Imirce
Department of Justice,
Home Affairs and Migration

# የእርስዎ መብቶች እና የመቀበያ ግዴታዎች



የሚከተሉት ሁኔታዎች የሚመለከቱዎት ከሆነ፣ ይህ መረጃ የተዘጋጀው ለእርስዎ ነው፡-

- እድሜዎ ከ18 አመት በታች ከሆነ
- እዚህ ከአንድ ወይም ከሁለቱም ወላጆችዎ ጋር ደርሰዋል
- እርስዎና ቤተሰብዎ በ *አይርላድ ውስጥ ለጥገኝነት (ዓለም አቀፍ ጥበቃ ተብሎም ይጠራል) አመልክታቹዋል።*

AMHARIC

# ይዘቶች


እርስዎና ቤተሰብዎ በዚህ ሀገር ውስጥ ደኅንነታችሁ የተጠበቀ ነው 3

ማን ሊረዳዎት ይችላል? 3

እርስዎና ቤተሰብዎ ምን ያገኛሉ? 4

የጤና እንክብካቤ የማግኘት መብት 6

ሠራተኞችን ያሳውቁ 7

የተሻለ ጥቅም ምዘና ምንድን ነው? 8

የትምህርት መብት 8

የመሥራት መብት 9

የጥገኝነት ጠያቂ ሰነዳቹ 9

እርስዎና ቤተሰብዎ የት ትቆያላችሁ? 10

አንድ ሰው መጥፎ አድርጎ ቢይዝዎት ምን ማድረግ ይችላሉ? 11

እርስዎና ቤተሰብዎ ምን ዓይነት የመቀበያ (የመስተንግዶ) ግዴታዎች አሉባችሁ? 12

እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ ግዴታዎቻችሁን ባትፈጽሙ ምን ይሆናል? 13

ዓለም አቀፍ ጥበቃ ለማመልከት እና ወደ የአውሮፓ ህብረት (EU)+ ሀገራት ለመጓዝ የሚረዱ ደንቦች 14

እርስዎና ቤተሰብዎ ወደ ሌሎች ሀገራት ብትሸሹ ምን ይሆናል? 15

በአስተዳደሩ በተላለፈ ውሳኔ ካልተስማሙ እርስዎና ቤተሰብዎን ማን ሊረዳችሁ ይችላል? 16


አንዳንድ ድጋፎች ቢቀየሩ ምን ይሆናል? 16

የእውቂያ ዝርዝሮች 17

## እርስዎ እና ቤተሰብዎ በዚህ ሀገር ደኅንነታችሁ የተጠበቀ ነው

እርስዎና ቤተሰብዎ አደጋ ላይ ስለሆናችሁ ወደ ሀገራችሁ መመለስ እንደማትችሉ ለባለሥልጣኖች ነግራችዋል፣ እንዲሁም ለጥገኝነት አመልክታቹዋል። እርስዎና ቤተሰብዎ በአይርላድውስጥ ጥገኝነት ጠያቂዎች ናችሁ።

## ማን ሊረዳዎት ይችላል?



በአውሮፓ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሁሉ እንደ ሕፃን ይቆጠራል፣ እንዲሁም **ልዩ ድጋፍ** የማግኘት መብት አለው።

በዚህች ሀገር በሚቆዩበት ጊዜ፣ ለምሳሌ የሚከተሉት ባለሙያዎች ሊረዱዎት ይችላሉ፡-

- **ማህበራዊ ሰራተኛ** በዕለት ተዕለት ፍላጎቶችዎ ላይ መርዳት ወይም በልዩ ችግር ላይ የሚያግዙ ሌሎች ባለሙያዎችን ማነጋገር ይችላሉ።
- ህመም ከተሰማዎ፣ ከቆሰሉ ወይም ማንኛውም አይነት የህክምና ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ፣ አንድ **ሀኪም** ወይም **ነርስ** ይረዳዎታል።
- ካዘኑ፣ ከተበሳጩ፣ ከተናደዱ፣ ከፈሩ ወይም እንቅልፍ እምቢ ካለዎት፣ አንድ **የስነ ልቦና ባለሙያ** ያግዝዎታል።
- **የሕግ አማካሪው** በጥገኝነት ሂደት ወቅት ምን እንደሚፈጠር እና መብቶቻችሁ እንዳልተጠበቁ ካመናችሁ እርስዎና ቤተሰብዎ እንዲረዱ ይረዳዎታል።
- **አስተርጓሚ** እርስዎ በሚረዱት ቋንቋ እንዲግባቡ ይረዳዎታል። የነሱ ሚና እርስዎ እና ሌሎች የተናገሩትን በትክክል መተርጎም ነው።


ችግር አለብዎት? ሁልጊዜም ድጋፍ እና እገዛ ለማግኘት ሰራተኞችን መጠየቅ ይችላሉ። አይጨነቁ፣ ችግሮች በጋራ ሊፈቱ ይችላሉ።

## እርስዎና ቤተሰብዎ ምን ያገኛሉ?

ባለሥልጣናት የጥገኝነት ማመልከቻችሁን በሚመረምሩበት ጊዜ የተለያዩ ዓይነት ድጋፍና አገልግሎቶችን ታገኛላችሁ። ይህ **መቀበያ (መስተንግዶ)** ይባላል።

እንደ ሕፃን እና እንደ ጥገኝነት ጠያቂ መብቶች አሉዎት፣ ነገር ግን ልታከብሯቸው የሚገቡ ግዴታዎችም አሉ። እነዚህ በዚህ መግለጫ ውስጥ ተብራርተዋል።

የዚህን መግለጫ ክፍሎች ካልተረዱ ወይም ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ ሠራተኞችንና ወላጆችዎን ይጠይቁ።



በዚህች ሀገር በሚቆዩበት ጊዜ፣ ሠራተኞቹ እንደ ሁኔታችሁ ተጨማሪ መረጃ ይሰጧችኋል። በማንኛውም ጊዜ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይችላሉ።

**በሁኔታችሁ ላይ ተመስርቶ፣ እርስዎና ቤተሰብዎ የሚከተሉትን ታገኛላችሁ፡-**



- የሚያድሩበት/የሚተኙበት ቤት/ቦታ



- ምግብ



- ልብስ



- የግል ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች



- ቤተሰብዎ ለዕለት ተዕለት ወጪ የሚሆን ገንዘብ ሊያገኙም ይችላሉ።

## የጤና እንክብካቤ መብት

**ባለሥልጣናት የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ ማግኘትዎን ያረጋግጣሉ።**

**ያለብዎትን ማንኛውንም የጤና ችግር ለቤተሰብዎ እና ለሠራተኞቹ ማሳወቅ ይችላሉ።** አስፈላጊ ከሆነ ነርስ ወይም ሐኪም እንዲያዩ ይረዱዎታል።



ሐኪሙ አስፈላጊ ነው ብለው ካመኑ፣ መድሃኒቶችን እንዲሁም ስፔሻሊስቶችን ለማየት የሚያስችሉ ቀጠሮዎችን ይሰጣሉ።

ከነርስ ወይም ከሐኪም ጋር የሕክምና ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋቹዋል እንደሆነ ሠራተኞቹ እርስዎንና ቤተሰብዎን ያሳውቃሉ።

ጤናዎን ሊመረምሩ እና አስፈላጊውን እርዳታ ሊሰጡዎት ይችላሉ።

ድንገተኛ የጤና ችግር ወይም አስቸኳይ ህክምና የሚያስፈልገው ጉዳት ካለብዎ ለወላጆችዎ ወይም ለሠራተኞቹ ይንገሩ። ከሚቆዩበት ቦታ ውጭ ከሆኑ፣ አስቸኳይ የስልክ ቁጥር 112 በነፃ መደወል ይችላሉ።

## ለሠራተኞቹ ያሳውቁ፤ የሚከተለው ከሆነ፡-







- ጤንነት ካልተሰማዎ፣ ከተጎዱ ወይም አስቸኳይ የሕክምና እርዳታ ወይም መድሃኒት የሚያስፈልግዎ ከሆነ
- ዕፅ ወይም አልኮል የሚጠቀሙ ከሆነ
- ቀደም ሲል ጥቃት ወይም በደል ደርሶብዎ ከነበረ ወይም አሁን እየደረሰብዎ ከሆነ
- እርጉዝ ከሆኑ ወይም ሊሆኑ ከቻለ
- በራስዎ መራመድ ካልቻሉ፣ ወይም የመስማት ወይም የማየት ችግር ካለብዎ
- በጣም ከተጨነቁ፣ ካዘኑ፣ መተኛት ካልቻሉ ወይም አሉታዊ ሐሳቦች ካለብዎ
- ደህንነትዎ እንዳልተጠበቀ ሆኖ ከተሰማዎ ወይም ከማንም ሰው (ከማያውቁትም ሆነ ከሚያውቁት) የሚፈሩ ከሆነ
- የማትፈልጉትን ነገር እንድታደርጉ ተገድዳችኋል ወይም እየተገደዳችሁ ነው
- በሃይማኖታችሁ፣ በፍቅር ምርጫዎ፣ በአለባበሳችሁ ወይም በባህሪያችሁ ምክንያት ደህንነት አይሰማችሁም
- የቤተሰብዎ አባላት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ።



## የተሻለ ጥቅም ምዘና ምንድን ነው?



ጥያቄዎችን የሚጠይቁዎት ሌሎች ሠራተኞችን የሚያዩበት ተግባር ነው። ዓላማውም:-

- **ፍላጎቶችዎን** ለመረዳት
- የሚያስፈልገዎትን **ድጋፍ ለመወሰን ነው።**

ይህ ባለሥልጣናት እርስዎና ቤተሰብዎ የት እንደሚቆዩን የመሳሰሉ አስፈላጊ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ይረዳቸዋል።

ነርሷን፣ ሐኪሙንና ሠራተኞችን ማመን ይችላሉ። ማንኛውንም ነገር ከእነርሱ ጋር መካፈል ይችላሉ። በፍቃድዎ ካልሆነ በስተቀር የሚሉት ነገር ከወላጆችዎ ውጪ ለማንም ሰው አይጋራም። ብቸኛው ልዩነት የእርስዎ ወይም የሌላ ሰው ሕይወት አደጋ ላይ ከሆነ ነው።

## የትምህርት መብት



እንደ ልጅ የትምህርትና የመማር መብት አላቸህው። ትምህርት ቤት እየሄዱ በዚህ ጊዜ ውስጥ 18 ዓመት ከሞላዎት፣ ትምህርቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ መቀጠል ይችላሉ።

ሠራተኞቹ እርስዎንና ቤተሰብዎን በአካባቢው ትምህርት ቤት እንዲመዘገቡ ይረዳሉ። ስለ ቅድመ-ዝግጅት ቋንቋ ትምህርቶች እና ሌሎች ኮርሶች ያሳውቁዎታል።

ሠራተኞቹ እንዲማሩ፣ እንዲያድጉ እና አዲስ ጓደኞችን እንዲያፈሩ የሚረዱዎትን የትምህርት እና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎችን ይነግሩዎታል።

## የመሥራት መብት





በእድሜዎና በሁኔታዎ ላይ ተመስርቶ ከፈለጉ በ አይርላድ መስራት ሊፈቀድልዎ ይችላል ፣ ከፈለጉ። ሠራተኞቹ ተጨማሪ መረጃ ይሰጡዎታል።



ከ 14 ዓመት በታች የሆኑ ሁሉም ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንዲሠሩ አይፈቀድላቸውም።

## የጥገኝነት ጠያቂ ሰነዶቻቹ



ከተመዘገቡ በኋላ፣ ማመልከቻዎ መቅረቡንና መመዝገቡን የሚያረጋግጥ ይፋዊ ሰነድ ይሰጥዎታል።

ማመልከቻዎን በይፋ ካስገቡ በኋላ፣ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች መሆንዎን የሚያረጋግጥ ይፋዊ ዲጂታል ሰነድ ይሰጥዎታል።

ይህ ሰነድ የዓለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ማረጋገጫ ተብሎ ይጠራል፣ እና በስልክዎ ውስጥ ማስቀመጥ ይችላሉ።

ይህን ሰነድ ሁልጊዜ ከእርስዎ ጋር መያዝ አለብዎት።

## እርስዎና ቤተሰብዎ የት ትቆያላችሁ?

ባለሥልጣናት የጥገኝነት ማመልከቻችሁን በሚመረምሩበት ጊዜ የምትቆዩበት ቦታ በሁኔታችሁ ላይ ይመሰረታል።



ሠራተኞቹ **ሁላችሁም የት መቆየት እንዳለባችሁ፣** ለምሳሌ በተወሰነ መጠለያ፣ ከተማ ወይም ክልል ውስጥ እንደሆነ ያሳውቋችኋል።

ይህ በሚገኙት ቦታዎች ወይም በቤተሰብዎ ፍላጎቶች ላይ ሊመሰረት ይችላል።

ቤተሰብዎ ከመጠለያው ውጭ ለመቆየት ወይም ለአጭር ጊዜ ከተማውን ወይም ክልሉን ለቅቆ መሄድ ከፈለገ፣ ከባለሥልጣኖች ፈቃድ መጠየቅ አለባቸው።

**እርስዎና ቤተሰብዎ ድጋፍና አገልግሎቶችን የምታገኙት ባለሥልጣናት በወሰኑበት ቦታ ብቻ ይሆናል ይችላል።**

ቤተሰቦች በፈለጉት ጊዜ መውጣትና መግባት ወደማይችሉበት ማዕከል የሚገቡት እጅግ በጣም አልፎ አልፎ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከሆናችሁ፣ የሕግ አማካሪ እና ሠራተኞቹ ይረዱዎታል።

**የትም ተመድባችሁ ብትቆዩ የሚከተሉትን መብቶች አላችሁ:-**



- **ከቤተሰብዎ ጋር ይቆዩ**



- **የቤተሰብዎ አባላት የት እንዳሉ የማያውቁ ከሆነ እነሱን ለመፈለግ እርዳታ ያግኙ።**

**በደህንነት የመኖር መብት አልዎት። ማንም ሰው እንዲህ እንዲያደርግ አይፈቀድለትም፡**




እንዲዝትብዎ እንዲሰድብዎ ጉዳት ሲያደርስብዎት

ማንም ይሁኑ ማን፣የማያውቁት ወይም የሚያውቁት ሰው።


ከወላጆችዎ ወይም ከሠራተኞቹ ጋር ማንኛውም ችግር ካለብዎ መናገር ይችላሉ።

## አንድ ሰው መጥፎ አድርጎ ቢይዝዎት ምን ማድረግ ይችላሉ?



የምትተማመኑት ሰው፣ የቤተሰብ አባል፣ የሠራተኛ አባል ወይም የመኖሪያ ማዕከልዎ ሰራተኛ

አንድ ሰው መጥፎ አድርጎ ቢይዛችሁ፣ ዳግመኛ እንዳይከሰት ለመከላከል ለባለሥልጣኖች ማሳወቅ ትችላላችሁ። ይህ 'ቅሬታ ማቅረብ' ይባላል።



**ትኩረት!**

ከሚቆዩበት ቦታ ውጭ ሆነው አደጋ ላይ ከሆኑ፣ ከማንኛውም ስልክ በነፃ ወደ ብሔራዊው የድንገተኛ ቁጥር 112 መደወል ይችላሉ።

## እርስዎና ቤተሰብዎ ምን ዓይነት የመቀበያ (የመስተንግዶ) ግዴታዎች አሉባችሁ?

እውነትን መናገርና ከባለሥልጣናት ጋር መተባበርዎ አስፈላጊ ነው፣ ታሪኮን ለመናገር አንዳንዴ የሚያስፈራና ከባድ ቢሆንም እንኳ።

ሠራተኞቹ ሁኔታዎን ካወቁ ሊረዱዎት ይችላሉ።



እርስዎና ቤተሰብዎ የትም ቦታ ቢቆዩ፣ የሚከተሏቸው ህጎች ይኖራሉ። ለምሳሌ፣ ሌሎች ነዋሪዎችንና ሠራተኞችን ማክበር አለባችሁ፣ እና በፀጥታ ሰዓት። ጫጫታ መፍጠር የለባችሁም።

ሠራተኞቹ ህጎቹንና ህጎች ባልተጠበቁ ጊዜ የሚመጡ ውጤቶችን (ቅጣቶችን) ያብራሩልዎታል።

እርስዎና ቤተሰብዎ የሚከተሉትን ማድረጋችሁ በጣም አስፈላጊ ነው፡-

- ✅ የምትቆዩበትን ቦታ ሕግጋት ይከተሉ
- ❌ ባለሥልጣኖች እንድትቆዩ ከነገሯችሁ ቦታ አይሽሹ።
- ✅ ሠራተኞቹ የሚያስረዱዋችሁን የዚህን ሀገር ሕጎች ይከተሉ።

## እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ ግዴታዎቻችሁን ባትፈጽሙ ምን ይሆናል?



ይህ ከተፈጠረ፣ ለሠራተኞቹ በግልጽ በመናገር ሁኔታችሁንና ምክንያታችሁን ማስረዳት ትችላላችሁ።

ባለሥልጣናት ሁኔታውን ይገመግማሉ አንዳንድ እርምጃዎችን ለመውሰድ ከወሰኑ ወላጆችዎን ያሳውቃሉ።



ለምሳሌ፣ የቤተሰብዎ አባል ባለሥልጣናት ቤተሰቡ እንዲቆይ ከወሰኑበት መጠለያ፣ ከተማ ወይም ክልል ቢሸሽ፣ **ያ የቤተሰብ አባል የሚያገኘው ድጋፍ ሊቀንስ ይችላል።**



የቤተሰብዎ አባል የአመፅ ባህሪ የሚያሳይከሆነ፣ **ያ የቤተሰብ አባል የሚያገኘውን ድጋፍ ሊያጣ ይችላል።** ፖሊስ ሊጠራ ይችላል።

**እርስዎና ቤተሰብዎ አሁን የአውሮፓ ህብረት (EU)+ ሀገር በሆነችው አይርላድ, ውስጥ ትገኛላችሁ። የአውሮፓ ህብረት (EU)+ ሀገራት የሚከተሉት ናቸው:-**

- 27 የአውሮፓ ኅብረት (EU) አባል ሀገራት:- ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮኤሽያ፣ ሳይፐረስ፣ ቼኪያ፣ ዴንማርክ፣ ኢስቶኒያ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሃንጋሪ፣ ጣሊያን፣ ላቲቪያ፣ ሊቱዌኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ የአየርላንድ ሪፐብሊክ፣ ሮማኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬንያ፣ ስፔን፣ ስዊድን እና
- 4 ሌሎች ሀገራት:- አይስላንድ፣ ሊችተንስታይን፣ ኖርዌይ እና ስዊዘርላንድ።

## ለጥገኝነት ለማመልከት እና ወደ EU+ ሀገራት ለመጓዝ የሚረዱ ደንቦች

**ሠራተኞቹ IPO እነዚህን አስፈላጊ ሕጎች እርስዎና ቤተሰብዎ ያስረዳሉ። በማንኛውም ጊዜ ጥያቄዎችን ልትጠይቋቸው ትችላላችሁ።**



- እርስዎና ቤተሰብዎ በ አይርላድ ውስጥ መቆየት አለባችሁ እንጂ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት (EU)+ ሀገር መሸሽ የለባችሁም።
- ከእነዚህ አገሮች በአንዱ የቤተሰብ አባላት ካሉዎት፣ ባለሥልጣናቱ በቤተሰብ መገናኘት ላይ ስላሎት መብቶች ያሳውቁዎታል። ሸሽተው ብቻ አይሂዱ።

ከዚህ አገር ለመውጣት ያስቡ ይሆናል ወይም አንዳንድ ሰዎች እንድትሸሽ ሊያሳምኑዎት ይሞክራሉ ይሆናል። ይህ ለእናንተ አደገኛ ሊሆን ይችላል። እርስዎና ቤተሰብዎ IPAS በማነጋገር ሁኔታውን ማስረዳት ትችላላችሁ። IPAS ሊመክሯችሁ ይችላሉ።


- ብትሸሹ፣ በዚህ መግለጫ ውስጥ የተብራሩ አሉታዊ ውጤቶች ይኖራሉ። ለምሳሌ፣ በሌላኛው ሀገር አነስተኛ የመቀበያ ድጋፍ ታገኛላችሁ።

- ያስታውሱ፣ ባለሥልጣናት ሌላ ካልነገሯችሁ በስተቀር የጥገኝነት ማመልከቻችሁን ለመጀመሪያ ጊዜ የደረሳችሁበት የአውሮፓ ህብረት (EU)+ ሀገር ማስመዝገብ አለባችሁ።

- የጥገኝነት ማመልከቻችሁን የመመርመር ኃላፊነት ያለበት ከነዚህ ሀገራት አንዱ ብቻ ነው። በ አይርላድ ውስጥ ያሉት ባለሥልጣናት የትኛው ሀገር ለዚህ ኃላፊነት እንዳለበት ይነግሯችኋል።

ስለነዚህ ሂደቶች በተለያዩ መግለጫዎች (ብሮሹሮች) ይማራሉ።

## እርስዎና ቤተሰብዎ ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት (EU)+ ሀገር ብትሸሹ ምን ይሆናል?




**በ አይርላድ ውስጥ:-**

- የጥገኝነት አሰራርዎ ሊቆም ይችላል።

**በሌላኛው የአውሮፓ ህብረት (EU)+ ሀገር ውስጥ:-**

- ባለሥልጣኖቹ ወደ ለቀቃችሁት ከሄዳቹህበት የአውሮፓ ህብረት (EU)+ ሀገር ለመመለስ ሊወስኑ ይችላሉ።

እርስዎን መልሰው የመላክ ውሳኔን ባለሥልጣናቱ ካሳወቁበት ጊዜ ጀምሮ የተወሰኑ መብቶችን የማግኘት መብት አይኖርዎትም ለምሳሌ:-

- አንዳንድ የድጋፍ ዓይነቶችን አታገኙም፣ እንዲሁም
- እንድትሠሩ አይፈቀድላችሁም።

## ባለሥልጣናት በወሰኑት ውሳኔ ካልተስማማችሁ እርስዎና ቤተሰብዎን ማን ሊረዳችሁ ይችላል?



ከሕግ አማካሪ እርዳታ መጠየቅ ትችላላችሁ። የሕግ አማካሪ ማለት በዚህ ሀገር ውስጥ ያሉትን ሕጎች የሚያውቅ ሁኔታችሁን ሊያጠና እና ሊረዳችሁ የሚችል ሰው ነው።

ሠራተኞቹ መረጃና እርዳታ ሊሰጧችሁ ስለሚችሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያሳውቋችኋል።




የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኤጀንሲ (UNHCR) በማንኛውም ጊዜ ማግኘት ትችላላችሁ። ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር. (UNHCR) ሀገራቸውን ለቀው እንዲወጡ የተገደዱ ሰዎችን ይጠብቃል።

## አንዳንድ ድጋፎች ቢቀየሩ ምን ይሆናል?

ባለሥልጣናት በገጽ 14 ላይእንደተብራራው ባለው ሁኔታ ምክንያት አንድ የቤተሰብ አባል የሚያገኘውን ድጋፍ ለመገደብ ወይም ለመሰረዝ ከወሰኑ፣ ያ የቤተሰብ አባል አሁንም በግል ሁኔታውና ፍላጎቱ ላይ ተመስርቶ እርዳታ ያገኛል። አሁንም ሐኪም ወይም ነርስ ማየት፣ የሕክምና እርዳታ፣ አንዳንድ ድጋፍ እና ባለሥልጣናት በወሰኑበት ቦታ መኝታ ያገኛሉ።



ወደ ሌላ የአውሮፓ ህብረት (EU)+ ሀገር ስለሸሻችሁ ባለሥልጣናት ለእርስዎና ለቤተሰብዎ የሚሰጠውን የመቀበያ ድጋፍ ለመሰረዝ ሲወስኑ፣ አሁንም የምታገኙት የድጋፍ ዓይነት በሁኔታችሁና በፍላጎታችሁ ላይ ይመሰረታል።

አሁንም ትምህርት ቤት መሄድ ትችላለህ።

# የእውቂያ ዝርዝሮች

እርስዎና ቤተሰብዎ ማንኛውም ጥያቄ ካላችሁ ወይም በሚቆዩበት ጊዜ ድጋፍ ካስፈለጋችሁ፣ በሚከተሉት ውስጥ ከሚሠሩ ሠራተኞች ጋር መነጋገር ትችላላችሁ:-

### ተቀባይ ባለስልጣን

An Roinn Dlí agus Cirt, Gnóthaí Baile agus Imirce
Department of Justice, Home Affairs and Migration

International Protection Accommodation Service
Department of Justice, Home Affairs and Migration.
51 St Stephen's Green, Dublin 2, D02 HK52

Email: IPASinboc@justice.ie

### ሌላ አግባብነት ያለው ባለሥልጣን

An Oifig um Chosaint Idirnáisiúnta
International Protection Office

The International Protection Office
Department of Justice, Home Affairs and Migration

Website: https://ipo.irishimmigration.ie

### ሌላ አግባብነት ያለው ባለሥልጣን

TUSLA

TUSLA – The Child and Family Agency
The Brunel Building, Heuston South Quarter
Saint John's Road West, Dublin 8, D08 X01F

Website: Tusla - Child and Family Agency

ስለሚከተሉት ጉዳዮችም እነዚህን ድርጅቶች ማነጋገር ትችላላችሁ:-


### የሕክምና ድጋፍ



ድንገተኛ የሕክምና እርዳታ የሚያስፈልግ ከሆነ በነፃ 999 ወይም 112 ይደውሉና አምቡላንስ ይጠይቁ።

በአካባቢዎ ውስጥ አጠቃላይ የጤና ድጋፎችን ለማግኘት፣ በመጠለያ ማዕከልዎ ውስጥ ያሉትን ሰራተኞች ይጠይቁ ወይም በነፃ HSELive (1800 700 700) ይደውሉ እና የHSE የስደተኛ የጤና ቡድንን ያነጋግሩ።

## ሥነ-ልቦናዊና ማኅበራዊ ድጋፍ



የአየርላንድ ቀይ መስቀል ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች የተለያዩ የአእምሮ ጤና እና የደህንነት ድጋፎችን ያቀርባል። ለመረጃ እዚህ ይመልከቱ።

በኮርክ እና ኬሪ የሚገኘው የኤችኤስኢ የጤና አገልግሎት በአረብኛ እና በፋርሲ የመስመር ላይ ቪዲዮዎች ስለ አሰቃቂ ሁኔታ እና ፒኤስቲዲ፣ እንቅልፍን፣ ጭንቀትን እና ሌሎች ችግሮችን እንዴት ማስተዳደር እንደሚቻል ያብራራል። ለመረጃ እዚህ ይመልከቱ።

የኤችኤስኢ የጤና አገልግሎት ምክር ቤት (CIPC) ለማግኘት፣ ስለ ሪፈራል ከሐኪምዎ ጋር ይነጋገሩ።

የአይሪሽ የስደተኞች ምክር ቤት ካርታ ጥበቃ ለሚፈልጉ ሰዎች ድጋፍ የሚሰጡ ድርጅቶችን መረጃ ያሳያል።

## የህጻናት ጥበቃ



የሕፃናት ኦምቡድስማን

Ombudsman for Children

Millennium House, First Floor

52-56 Great Strand Street, Dublin 1, D01 F5P8

Website: https://www.oco.ie/

## አደጋ ላይ ላሉ ሕፃናት የእርዳታ መስመር



ችላ እንደተባሉ ወይም አደጋ ላይ እንዳሉ ከተሰማዎት 119 በነፃ መደወል ይችላሉ

Childline በማንኛውም ልጅ ወይም ወጣት በ1800 66 66 66 በመደወል ወይም በቀን ለ24 ሰዓታት በChildline.ie ላይ በመስመር ላይ በመወያየት ማግኘት ይቻላል።

ወንድምዎ፣ እህትዎ ወይም ጓደኛዎ ከጠፉ፣ የ116 000 - የጠፉ ሕፃናት አውሮፓ (Hotline 116 000 - Missing Children Europe) የስልክ መስመር መደወል ይችላሉ

## legal counselling, assistance and representation



የሕግ ምክር አገልግሎት በሲቲዌስት ኮንቬንሽን ሴንተር በሊግ ኤይድ ቦርድ ሲቲዌስት ኮንቬንሽን አገልግሎት በኩል ይቀርብልዎታል።

በሲቲዌስት ኮንቬንሽን ሴንተር ወይም ከእነዚህ 3 የሕግ ማዕከላት በአንዱ የሕግ ድጋፍ ቦርድ የሕግ ምክር እና ውክልና (የሕግ ድጋፍ) ማመልከት ይችላሉ፡:

1. **Dublin:** Smithfield Law Centre
   📞 (01) 646 9600
2. **Cork:** Popes Quay Law Centre
   📞 087 945 1132
3. **Galway:** Galway Law & Family Mediation Centre
   📞 091 568 467 / 01 646 9637

## ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር. UNHCR (የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኤጀንሲ፣ the United Nations Refugee Agency)

የጥገኝነት ጠያቂዎችን እና ስደተኞችን ጥቅም እና መብቶችን ይጠብቃል።




UNHCR, Merrion House, Suite 4, 1-3 Lower Fitzwilliam Street, Dublin 2, Ireland

Website: https://help.unhcr.org/.

Email: iredu@unhcr.org

Phone (Protection Unit): +353 1 631 4613

| | |
|---|---|
| የውህደት ድጋፍ | https://www.localgov.ie/lait-contact-details |
| ወደ ትውልድ አገርዎ ለመመለስ የሚደረግ ድጋፍ | voluntaryreturns@justice.ie |

ድንገተኛ የሕክምና ችግር ካለብዎ ወይም አደጋ ላይ ከሆኑ፣ እነዚህን ድንገተኛ ቁጥሮች በነፃ መደወል ይችላሉ፡-

**የሕክምና ድንገተኛ ሁኔታ፡- 112/999**

**ፖሊስ፡- 112/999**

euaa
EUROPEAN UNION
AGENCY FOR ASYLUM

An Roinn Dlí agus Cirt,
Gnóthaí Baile agus Imirce
Department of Justice,
Home Affairs and Migration

ይህ ብሮሸር ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም። የEUAA የዚህን ጽሑፍ ዋና ክፍል አቅርቧል፣ እና የዚህ መግለጫ ቅጂ ማውጣትና ማሻሻያ ማድረግ በEUAA የተፈቀደው ለአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ብቻ ነው። የEUAA በአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ወይም በሌላ ማንኛውም ኃላፊነት ባለው ሶስተኛ ወገን በዚህ ብሮሸር ውስጥ የተካተተው መረጃ ትክክለኛነት፣ ይዘት፣ ሙሉነት፣ ሕጋዊነት ወይም አስተማማኝነት ላይ ምንም ዓይነት ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነትን አይቀበልም። ይህ ብሮሸር ሊውልበት ስለሚችል ጥቅም የ EUAA ሆነ ማናቸውም በEUAA ስም የሚሰራ የትኛውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025